የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 587/2013

## ስለዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ

ሀገራችን ከዓለም አቀፍ ንግድ በተሻለ መልኩ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማስቻልና የዓለም አቀፍ ንግድ ድርጅት አባልነት ሂደትን ለማስተባበር፣ የአካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ሀገራዊ ጥቅምን ባስጠበቀ መልኩ ለማጠናቀቅ እንዲቻል አግባብ ያላቸው አካላትን በጋራ፣ በተቀናጀና ወጥነት ባለው ሁኔታ ማስተባበር ተገቢ በመሆኑ፤

የንግድ ግንኙነትና ድርድር አካል ሆነው በተለያዩ አስፈጻሚ አካላት ሲመሩ የነበሩ ጉዳዮችን የሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካል ተሰብስበው እንዲተዳደሩ በማድረግ በመስኩ የእውቀትና የክህሎት ሽግግር ማድረግና ብቁ የሰው ኃይልን በማፍራት ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የንግድ ግንኙነትና ድርድሮችን ከሀገራዊ ራዕይ ጋር በማስተሳሰር በመስኩ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት እንዲቻል በሚኒስትሮች ምክር ቤት አሠራር መመሪያ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት ይህ መመሪያ አውጥቷል።

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት መመሪያ ቁጥር 587/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1/ "ብሔራዊ ኮሚቴ" ማለት የንግድ ድርድር ጉዳዮችን በብሔራዊ ደረጃ ለመምራት እንዲያስችል በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱትን መሥሪያ ቤቶች ያቀፈ ኮሚቴ ነው፤

2/ "ቴክኒክ ኮሚቴ" ማለት ብሔራዊ ኮሚቴውን በቴክኒካዊ ጉዳዮች ለመደገፍ ከመንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች፣ ከንግድና የዘርፍ ማህበራት፣ ከከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት፣ ከሙያ ማህበራት እና በጉዳዩ ላይ ክህሎት ያላቸው ግለሰቦችን ያቀፈ እና እንደአስፈላጊነቱ በብሔራዊ ኮሚቴ የሚመደቡትን ያካተተ ኮሚቴ ነው፤

3/ "የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት ድርድር" ማለት ሀገሪቱ የዓለም ንግድ ድርጅትን ለመቀላቀል ከአባል ሀገራት ጋራ የሚደረግ ድርድር ነው፤

4/ "አካባቢያዊ ድርድር" ማለት አህጉራዊና ክፍለ አህጉራዊ ድርድሮችን እና ከሁለት በላይ ከሆኑ ሀገሮች ጋር የሚደረግ የንግድ ድርድር ሲሆን ከበይነ መንግስታት ልማት ባለስልጣን /ኢጋድ/፣ ከምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ /ኮሜሳ/፣ የምስራቅ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ፣ የደቡባዊ አፍሪካ የልማት ማህበረሰብና ኮሜሳ አባል ሀገራት የነጻ ንግድ ቀጣና ለመመስረት የሚያደርጉት የሶስትዮሽ

/ትራይፓይት/ እና በአፍሪካ አህጉር ደረጃ የሚካሄደውን የንግድ ድርድሮችን እንዲሁም የኢኮኖሚ አጋርነት ድርድሮችንም የሚያካትት ነው፤

5/ "የኢኮኖሚ አጋርነት ስምምነት ድርድር" ማለት ኢትዮጵያን ጨምሮ የምስራቅና የደቡባዊ አፍሪካ ሀገራት ቡድን ከአውሮፓ ህብረት ጋር ነጻ የንግድ ግንኙነት ለመመስረት የሚያደርጉት ድርድር ነው፤

6/ "አግባብነት ያላቸው አካላት" ማለት ብሔራዊ ኮሚቴ፣ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት የሚሰየሙባቸው፣ በዚህ መመሪያ ውስጥ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች በሚል የተገለጹት እና የመተባበር ግዴታ ያለባቸውን አካላትንም የሚያካትት ነው።

3. <u>ብሔራዊ ኮሚቴ ስለመቋቋም</u>

የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮች ጉዳዮችን በአገር አቀፍ ደረጃ የሚመራና የተለያዩ መሥሪያ ቤቶችን ያቀፈ ብሔራዊ አስተባባሪ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል።

4. <u>የብሔራዊ ኮሚቴ አሰያየም፣ ተጠሪነትና ስብሰባ</u>

1/ የብሔራዊ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ ዋና ተደራዳሪ እና ምክትል ዋና ተደራዳሪ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ሆነው የሚከተሉትን መሥሪያ ቤቶች የሚያካትት ይሆናል፤

ሀ) የንግድ ሚኒስቴር፤

ለ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤

ሐ) የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር፤

መ) የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፤

ሠ) የኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፤

ረ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፤

ሰ) የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ኢንስቲትዩት፤

ሸ) ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ በመንግስት የሚመደቡ መሥሪያ ቤቶች።

2/ የንግድ ሚኒስቴር የብሔራዊ ኮሚቴው ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል።

3/ የብሔራዊ ኮሚቴው በየሁለት ወሩ መደበኛ የስብሰባ ቀን ይኖረዋል፣ ሆኖም እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊጠራ ይችላል።

4/ የብሔራዊ ኮሚቴው አባላት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮችን እንደ ሌሎች መደበኛ ሥራዎቻቸው በመቁጠር በመሥሪያ ቤቶቻቸው ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ በማካተት ያከናውናሉ።

5/ የብሔራዊ ኮሚቴው አባል በመሥሪያ ቤቶቹ የበላይ ኃላፊዎች የሚወከሉ ሲሆን የበላይ ኃላፊዎቹ ለስራው ጠቀሜታ ያላቸው ከፍተኛ አመራሮችን በደብዳቤ ሊወክሉ ይችላሉ።

5. <u>የብሔራዊ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>

ብሔራዊ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ የሀገሪቱ የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮችን እንዲሁም በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድርድሮችና መርሐ-ግብሮችን ይነድፋል፣ ሂደቶቹንም ያስተባብራል፤

2/ በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ የሚካሄዱ የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት፣ የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነቶችንና ድርድሮችን ሀገሪቱን በመወከል ይደራደራል፤

3/ የእንድምታ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤

4/ የሕግ ወይም የፖሊሲ ለውጥ ማድረግ የሚያስፈልጋቸውን ንግድና ንግድ ነክ ጉዳዮች በመለየት መንግሥትን ያማክራል፤

5/ ለንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮች የሚያስፈልጉ የቴክኒክ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፤

6/ በቴክኒክ ኤክስፐርቶችና በሲኒየር ኦፊሺያሎች ደረጃ ለሚደረጉ ድርድሮች አስፈላጊ የሆኑ የመደራደሪያ ወሰኖች እና ተግባርና ኃላፊነቶችን ይወስናል፣ እንዲተገበሩም ያደርጋል፤

7/ ከቴክኒክ ኮሚቴው የሚቀርቡለትን ዝርዝር ሥራዎች እየገመገመ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ ከኮሚቴው በሚቀርቡ የድርድር አቋሞች ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በማማከር ውሳኔ ይሰጣል፤

8/ የንግድ ድርድር አቅም ግንባታ ለማካሄድ የሚያስችል ፕሮግራም በመንደፍ በየደረጃው አቅም እንዲገነባ ያደርጋል፤ የቴክኒክ ኮሚቴው አስፈላጊውን ተከታታይ ሥልጠና የሚያገኝበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፤

9/ ለድርድሮች አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶች እንዲመደቡ ያደርጋል፣ አጠቃቀማቸውንም ይወስናል፤

10/ የዓለም ንግድ ድርጅት እና አካባቢያዊ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮች ስለደረሱበት ደረጃና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች በየጊዜው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት ያቀርባል፤

11/ ለንግድ ግንኙነትና ድርድሮች አስፈላጊ የሆኑ ተግባራትን ሀገራዊ ጥቅምን ባስጠበቀ መልኩ በሥልጣን ገደቡ ውስጥ ያከናውናል፤

12/ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ይፈጽማል።

6. <u>የቴክኒክ ኮሚቴ ስለመቋቋም</u>

የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮች ጉዳዮች ላይ ለብሔራዊ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 መሠረት የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጥ የቴክኒክ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል።

7. <u>የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት</u>

1/ የቴክኒክ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለብሔራዊ ኮሚቴው ሆኖ፣ አባል መሥሪያ ቤቶች ወይም አደረጃጀቶች ወይም ግለሰቦች በብሔራዊ ኮሚቴው ቀጣይነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ በደብዳቤ የሚሰየሙ ይሆናል።

2/ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት ከሚከተሉት አካላት ተውጣጡ ይሆናሉ፤

ሀ) የንግድ ሚኒስቴር ----------------------------------------ሰብሳቢ፤

ሀ) የብሔራዊ ኮሚቴ አባላት ከሆኑ መሥሪያ ቤቶች ------አባል፤

ለ) ከሌሎች ከተመረጡ የመንግስት መስሪያ ቤቶች --------አባል፤

ሐ) ከንግዱ ማህበረሰብ-----------------------------------------አባል፤

መ) ከሞያ ማህበራትና ከአካዳሚ ማህበረሰብ-----------------አባል፤

ሠ) በጉዳዩ ላይ ክህሎት ያላቸው ግለሰቦችን -----------አባል፤እና

ረ) እንደ አስፈላጊነቱ በብሔራዊ ኮሚቴው ከሚመደቡ አባል።

8. <u>የቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት</u>

የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት የዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና የአካባቢያዊ ንግድ ግንኙነትና ድርድር ጉዳዮችን እንደ ሌሎች መደበኛ ሥራዎቻቸው በመቁጠር በመሥሪያ ቤቶቻቸው ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተት ያደርጋሉ፤

2/ የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት በኮሚቴው ውስጥ የሚሰጣቸውን ሀላፊነቶች በወቅቱ ሀገራዊ ጥቅምን ባስጠበቀ መልኩ ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፤

3/ ሥራውን የሚያካሂድበት መርሐ-ግብርና የሚተዳደርበትን የአሰራር ሥርዓት በመቅረጽ ለብሔራዊ ኮሚቴው በማቅረብ ያስወስናል፣ በውሳኔው መሠረትም ያስፈጽማል፤

4/ ለሥራው ውጤታማነትና ቅልጥፍና የሚያስፈልጉ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ሊያዋቅር ይችላል፤

5/ የዓለም ንግድ ድርጅት መቀላቀል እና አካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮችን እንዲሁም በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ተግባራት በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ሊያሳድሩ

የሚችሉትን እንድምታ ጥናቶች ያካሂዳል፣ እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች አካላት እንዲጠኑ ያደርጋል፣ በሌሎች የቀረቡ ጥናቶችን ይገመግማል፤ በጥናቶቹ ግኝቶች ላይ በመመስረት የድርድር ሃሳቦችን ያቀርባል፤

6/ ለዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና አካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮች አስፈላጊ የድርድር ሰነዶችን ያዘጋጃል፤

7/ ለዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና አካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶች እና ለሚደረጉት ድርድሮች የኢትዮጵያን አቋም በማዘጋጀት ያቀርባል፤

8/ በቴክኒክና በሲኒየር ኦፊሺያል ደረጃ የሚካሄዱ ድርድሮችን ይደራደራል፤

9/ ከድርድሮቹ ጋር በተያያዘ አዲስ ሕግ ማውጣት ወይም የነበረውን ማሻሻል ሲያስፈልግ ረቂቅ ሕግ በማዘጋጀት ለብሔራዊ ኮሚቴው ያቀርባል፤

10/ ንግድና ንግድ ነክ ፖሊሲዎች ላይ አስተያየቶችንም ያዘጋጃል፤

11/ በማናቸውም አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የሚወጡ ንግድና ንግድ ነክ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ከመጽደቃቸው በፊት ከሚካሄዱት ድርድሮች ጋር መጣጣም ያለመጣጣማቸውን እያረጋገጠ ለአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች ግብአት ይሰጣል፤

12/ የንግድ ግንኙነትና ድርድር ሥራዎች በተመለከተ የተከናወኑ ተግባራት ለብሔራዊ ኮሚቴው በየወቅቱ ዝርዝር ሪፖርት ያቀርባል፤

13/ ለንግድ ግንኙነት ለድርድር የሚጠቅሙ ማናቸውንም ጉዳዮች በሥልጣን ወሰኑ ውስጥ የሀገሪቱን ጥቅም ሊያስጠብቅ በሚችል ደረጃ ያከናውናል፤

14/ ከብሔራዊ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ማንኛውንም ተግባራት ያከናውናል።

9. <u>የሴክሬቴሪያቱ ተግባርና ኃላፊነት</u>

የብሔራዊ ኮሚቴው ሴክሬታሪያት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1/ ከውጭ ሀገራት ጋር የሚደረጉ ማንኛውንም የንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮችን ያካሂዳል፤

2/ የብሔራዊና የቴክኒክ ኮሚቴ ስብሰባዎች የሚካሄዱበትን ቦታዎች፣ የስብሰባ አጀንዳዎችና ሰነዶችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

3/ የድርድሮቹን ሂደት በሚመለከት ከየትኛውም አካላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፣ ስለድርድሮቹ ሂደት በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥርዓት በመዘርጋት ያካሂዳል፤

4/ ዝርዝር የጥናት ውጤቶችን መሰረት በማድረግ የድርድር ሰነዶች ለብሔራዊ ኮሚቴው ያቀርባል፤

5/ የቴክኒክ ኮሚቴው ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፣ የንግድ ግንኙነት እና የድርድር ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፤

6/ የንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮች በተቀናጀ አግባብ የሚመሩበት ኘሮግራሞችን ይነድፋል፣ ኘሮጀክቶችን ያደራጃል፣ ተግባራዊም ያስደርጋል፤

7/ ለንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮች የተመደቡ ሀብቶችን አጠቃቀም መርሀ-ግብሮችን ይነድፋል፣ ሪፖርቶችንም ያቀርባል፤

8/ ለንግድ ግንኙነቶችና ድርድሮች የሚያስፈልጉ ሌሎች ማናቸውንም ተግባራት ያከናውናል፤

10. <u>ተደራዳሪዎችን ስለመሰየም</u>

1/ በዓለም ንግድ ድርጅት አባልነት እና በአካባቢያዊ የንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮች ዋና ተደራዳሪ እና ምክትል ዋና ተደራዳሪ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሰየማል።

2/ ዋና ተደራዳሪው ከምክትል ተደራዳሪውና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር እንደ ድርድሩ አይነትና አካሄድ ሌሎች ረዳት ተደራዳሪ አባላትን ይመድባል።

11. <u>የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የመንግስት መሥሪያ ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፤

1/ ለንግድ ግንኙነቶች እና ድርድሮቹ ስኬት ብሔራዊ ኮሚቴው ለሚጠይቃቸው ጉዳዮች በባለቤትነት የተሟላና ወቅታዊ ምላሽ የመስጠት፤

2/ ለቴክኒክ ኮሚቴ አባልነት የሚመረጡ የሥራ ኃላፊዎች የመደበኛ ሥራቸው አካል በማድረግ በቋሚነት መድቦ እንዲሰሩ የማድረግ።

12. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም መንግስታዊ አካል ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የሚከናወኑ ተግባራትን ለማከናወን የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ መረጃ በመስጠት፣ ባለሙያዎችን በማሳተፍ፣ ሥራዎቹን የእቅዱ አካል በማድረግ፣ የሚወጡ ንግድ ነክ ሕጎችን በረቂቅ ደረጃ የማቅረብ፣ በእነዚህ ላይ የሚሰጡ አስተያየቶችን የማካተት እና ሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ለሀገራዊ ጥቅም ሲባል የመተባበር ግዴታ አለበት።

13. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1/ ከዚህ መመሪያ መጽደቅ በፊት በሌሎች አግባብ ያላቸው አካላት ሲደረጉ የነበሩ የአካባቢያዊ የንግድና ንግድ ነክ ጉዳዮች ግንኙነቶችና ድርድሮች ባሉበት ደረጃ ወደ ንግድ ሚኒስቴር የሚተላለፉ ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሠረት የሚያስተላልፉ አግባብ ያላቸው አካላት ለንግድ ግኑኙነትና ድርድር ሂደቶች ቀጣይነት የበኩላቸውን ኃላፊነትና ትብብር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

14. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሽል ወይም ሊለውጥ ይችላል፡፡

15. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች እና አሠራሮች</u>


1/ የዓለም ንግድ ድርድር ጉዳዮችን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 1/2003 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

2/ ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የልምድ አሠራር በዚህ መመሪያ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይኖረውም፡፡

16. <u>የመመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከዛሬ ሐምሌ 07 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ 07 ቀን 2009 /2009




የሚኒስትሮች ምክር ቤት